# ዕቃዎች በጊዜያዊነት አገር ውስጥ የሚገቡበትና በአገር ውስጥ ስለሚቀሩበት ሁኔታ እና የቀረጥና ታክስ ክፍያ አፈፃፀም

## <u>መመሪያ ቁጥር 28/2002</u>

የጉምሩክ አዋጅ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር የሚገቡበት እና በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች በአገር ውስጥ የሚቀሩበት ሁኔታ እንዲሁም የቀረጥ ክፍያው አፈፃፀም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ፣

አገሪቱ የተያያዘችውን የልማት አቅጣጫ ለመደገፍ ይረዳ ዘንድ በተለያዩ ምክንያቶች ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ በሕግ የተፈቀደ በመሆኑና ከእነዚህ ዕቃዎች ውስጥ በአገር ውስጥ እንዲቀሩ የሚፈቀደውን ዕቃዎች ዓይነት፣ አገር ውስጥ ስለሚቀሩበት ሁኔታና የቀረጥና ታክስ ክፍያውን አፈፃፀም ስርዓት ወጥ በሆነ መልኩ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 54 (2) እና (9) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ «ዕቃዎች በጊዜያዊነት አገር ውስጥ የሚገቡበትና በአገር ውስጥ የሚቀሩበትን ሁኔታ እና የቀረጥና ታክስ ክፍያ አፈፃፀም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 28/2002» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፣

1. «ዕቃ» ማለት በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት እና በዚህ መመሪያ መሠረት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባ ዕቃ ነው።

2. «አስመጪ» ማለት በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት ዕቃዎችን በጊዜያዊነት ያስገባ ሰው ነው::

3. «ሰው» ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው::

4. «ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ» ማለት አገልግሎት ከመስጠት ጋር ባልተያያዘ በጊዜያዊነት በገባ ዕቃ ላይ የሚደርስ ድንገተኛ አደጋ ወይም ጉዳት ነው::

5. «ባለሥልጣን» ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው::

6. «ሚኒስትር» ወይም «ሚኒስቴር» ማለት የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ነው::

7. «አዋጅ» ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው::

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት በጊዜያዊነት ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::



# ክፍል ሁለት

# ዕቃዎች በጊዜያዊነት አገር ውስጥ ስለሚገቡበትና በአገር ውስጥ ስለሚቀሩበት ሁኔታ

## 4. በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች

በአዋጁ አንቀፅ 54 (ለ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ::

1. በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከሚጠበቅ ኃላፊነት ጋር በተያያዘ ለሰላም ማስከበር ወይም ሌላ ተልዕኮ የሚውሉ፣

2. ለዓለም ዓቀፍ ስብሰባ፣ ኮንፈረንስ፣ ሲምፖዚየም ወርክሾፕ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች፣

## 5. <u>በአገር ውስጥ መቅረት የሚችሉ ዕቃዎች</u>

1. ከንግድ ማስተዋወቅ፣ከቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ከቱሪዝምና ከባሕል ልውውጥ፣ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከሚጠበቅ ኃላፊነት ጋር በተያያዘ ለሰላም ማስከበር ወይም ሌላ ተልዕኮ የሚውሉ፣ እንዲሁም ለዓለምዓቀፍ ስብሰባ፣ ኮንፈረንስ፣ ሲምፖዚየም፣ ወርክሾፕ አገልግሎት የሚውሉ፣ በጊዜያዊነት ወደ አገር የሚገቡትን ዕቃዎች ሳይጨምር ከግንባታ ሥራና ከምክር አገልግሎት ወይም በፕሮጀክት ስምምነት መሠረት ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 (1) ድንጋጌ መሠረት ጥያቄ ሲቀርብ በአገር ውስጥ እንዲቀሩ ባለስልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ቢኖርም፣

   ሀ. ንግድን ከማስተዋወቅ፣ ከቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ከቱሪዝምና ከባሕል ልውውጥ ጋር በተያያዘ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባው ዕቃ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ከአገልግሎት ውጪ መሆኑን ባለሥልጣኑ በበቂ ማስረጃ ካረጋገጠ፣

3

   ለ. ንግድን ለማስተዋወቅ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባው ዕ ዒታደል በመሆኑ ወይም ለመንግስት መ/ቤቶች በነፃ እንዲሰጥ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተፈቀደ እንደሆነ፣ አገር ውስጥ እንዲቀር ሊፈቀድ ይችላል፡፡

## 6. <u>ስለ ማመልከቻ አቀራረብ እና ውሣኔ አሰጣጥ</u>

1. በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባን ዕቃ በአገር ውስጥ እንዲቀር የፈለገ አስመጪ ጥያቄውን በፅሁፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2. ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ላይ ከተገለፁት እቃዎች ጋር በተያያዘ ማመልከቻ ሲቀርብለት፣

ሀ. ጥያቄው የቀረበው ዕቃው በአገር ውስጥ እንዲቆይ በተፈቀደው ወይም በፕሮጀክት ስምምነቱ ውስጥ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መሆኑን፣ እና

ለ. አግባብ ካለው መስሪያ ቤት በአገር ውስጥ እንዲቀር ፈቃድ የተሰጠበት ማስረጃ መኖሩን፣ ወይም

ሐ. ዕቃው በአገር ውስጥ እንዲቀር የተጠየቀበት ምክንያት በዕቃው ላይ ከደረሰ ጉዳት ጋር በተያያዘ እንደሆነ ዕቃው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ከአገልግሎት ውጪ ስለመሆኑ አግባብ ካለው መስሪያ ቤት የተሰጠ ማረጋገጫ መቅረቡን፣

በማረጋገጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

# ክፍል ሶስት

# ስለ ቀረጥና ታክስ ክፍያ አፈፃፀም

## 7. መሠረቱ

በዚህ መመሪያ መሠረት በአገር ውስጥ እንዲቀር ፈቃድ የተሰጠው በጊዜያዊነት የገባ ዕቃ ከዚህ በታች በአንቀፅ 8 በተደነገገው መሠረት ቀረጥና ታክስ ይከፈልበታል፡፡



## 8. የቀረጥና ታክስ አከፋፈል

1. ከግንባታ ሥራና ከምክር አገልግሎት ወይም በፕሮጀክት ስምምነት መሠረት ወደ አገር የገባ ዕቃ በአገር ውስጥ እንዲቀር በባለሥልጣኑ ሲፈቀድ ዕቃው ሲገባ በሚያወጣው ዋጋ፣ ለዕቃዎቹ ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ዲክላራሲዮን ቀርቦ ተቀባይነት ባገኘበት ዕለት ባለው የገንዘብ ምንዛሪ እና የታሪፍ ልክ (Rate) ቀረጥና ታክስ ይከፈልበታል፡፡

2. በጊዜያዊነት የገባ ዕቃ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ከአገልግሎት ውጪ በመሆኑ በአገር ውስጥ እንዲቀር ለባለሥልጣኑ ጥያቄ ሲቀርብ በእቃው የእርጅና ዋጋ ላይ የሚከፈለው የአገልግሎት ቀረጥና ታክስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመድን ድርጅት ወይም ከመንገድ ትራንስፖርት ወይም ፈቃድ ከተሰጣቸው በግምት ስራ ላይ ከተሰማሩ ድርጅቶች በሚቀርበው የጉዳት ሪፖርት መሠረት የጉዳቱ መጠን ተቀንሶ በሚያወጣው ዋጋ ለእቃዎቹ ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ዲክላራሲዮን ቀርቦ

ተቀባይነት ባገኘበት ዕለት ባለው የገንዘብ ምንዛሪ እና የታሪፍ ልክ መሠረት ቀረጥና ታክስ ይከፈልበታል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ላይ የተደነገገው ቢኖርም በዕቃው ላይ የደረሰው ጉዳት ዕቃውን ሙሉ በሙሉ ከአገልግሎት ውጪ ያደረገው እንደሆነ ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ባለው የእርጅና ቅናሽ ስሌት መመሪያ መሠረት የአገልግሎት (የእርጅና ቅናሽ) ላይ ቀረጥና ታክስ ይከፈላል፡፡

## 9. የአፈፃፀም መመሪያ ስለማውጣት

ባለሥልጣኑ ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም የሚረዳ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 10. የተሻሩ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች

ይህን መመሪያ የሚቃረኑ መመሪያዎች ሰርኩላሮች እና የአሰራር ስርዓቶች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## 11. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታህሣሥ 5 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሣሥ 2 ቀን 2002 ዓ.ም

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር